# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የባህል ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ የኮቪድ-19 ጥንቃቄ እና ደህንነት አጠባበቅ

## መመሪያ ቁጥር 810/2013

# መመሪያ ቁጥር 810/2013
# <u>በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር</u>
# <u>የባህል ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ የኮቪድ-19</u>
# <u>ጥንቃቄና ደህንነት አጠባበቅ መመሪያ</u>

የኮሮና ወረርሽኝ በሀገራችን መከሰቱን ተከትሎ በባህል ዘርፍ በተለይም በእይታዊ፣ በትዕይንታዊ (ክውን) በስነ-ጽሁፋዊ ጥበባት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር በሀገራችን ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ቀውስ በማስከተሉ፤

በወረርሽኙ ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የባህል ተቋማት አገልግሎት ጥንቃቄ በተመላበት መልኩ እንደገና በማስጀመር ያጋጠመውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን መቅረፍ በማስፈለጉ፤

የባህል ተቋማት አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ተገቢውን የደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን በመከተል አሰራራቸውን በተደራጀ መንገድ በማዘመን አገልግሎቱ ከስጋት በጸዳ አግባብ መምራት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 30 ንዑስ ቁጥር 2 የባህል ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ደህንነትን በማስጠበቅ ለማስፋፋት በማሰብ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ “የባህል ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ የኮቪድ-19 ጥንቃቄና ደህንነት አጠባበቅ መመሪያ ቁጥር 810/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **“የባህል ተቋማት”** ማለት ለሥነ-ጽሁፋዊ፣ ዕይታዊ እና ትዕይንታዊ ጥበባት አገልግሎት የሚሰጡ አብያተ-መፅሀፍት፣ የሲኒማ ቤቶች፣ ቴአትር ቤቶች፣ የባህል ማዕከላት፣ ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ ስራዎች የሚቀርቡባቸው ቦታዎች ወይም መድረኮች እንዲሁም ቤተ መዘክሮች እና ጋለሪዎች ናቸው፡፡

2) **“ጥበባት”** ማለት የሰው ልጅ እውቀት፣ ልምድና ክህሎቱን ተጠቅሞ በፈጠራ አስውቦ የሚሠራው ዕይታዊ ጥበብ፣ ትውን ጥበብ እና ጽሑፋዊ ጥበብ ነው፡፡
3) **“ትዕይንት ማሳያ ተቋም”** ማለት ትያትር ቤት፣ ሲኒማ ቤት፣ ባህል ማዕከል፣ የባህል አዳራሽ እና የባህላዊ ምሽት ቤት ነው፡፡
4) **”ተገልጋይ”** ማለት የጥበብ አቅራቢ፣ አንባቢ፣ የትዕይንት ታዳሚና ጎብኚ ነው፡፡
5) **”ከበራ”** ማለት በአደባባይ፣ በቅጥር ወይም በተቋም ውስጥ የሚከወን የባህላዊ ይዘት ያለው የበዓል ትዕይንት ነው፡፡
6) **“አካላዊ መራራቅ”** ማለት የኮቪድ-19 በሽታ ከሰው ወደ ሰው የሚኖረውን ስርጭት ለመቀነስ ወይም ለመግታት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይም ሁለት ሜትር እና ከዛ በላይ ርቀትን መጠበቅ ነው፡፡
7) **“ፀረ-ተህዋስ”** ማለት በምግብ እና መድሃኒት ቁጥጥር ባለሰልጣን የተረጋገጠ የኮቪድ-19 ቫይረስን ከህንፃ ግድግዳ፣ ከአዳራሽ፣ ከበር እና መስኮቶች እንዲሁም ከቁሳቁሶች ላይ ለማፅዳት የሚውል ፈሳሽ ኬሚካል ነው፡፡
8) **“ሚኒስቴር”** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡
9) **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተውን ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡
10) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
11) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## 3. <u>ዓላማ</u>

በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የተቋረጠውን የባህል ተቋማት አገልግሎት ተገቢውን የደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን በማክበር የሚጀመርበትን አግባብ ለመፍጠር የሚያስችል ወጥ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## 4. <u>መርሆዎች</u>

ይህን መመሪያ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚከተሉትን መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

1) የባህል ተቋማት አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ተገቢውን የደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የማክበር፣

2) በአገልግሎ አሰጣጥ ሂደት በመመሪያው የተጠቀሱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በፍጹም ተጠያቂነትና ትጋት በማክበር ተግባራቸውን ማከናወን፤

5. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገራችን ውስጥ ባሉ የባህል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የባህል ተቋማትና የተገልጋዮች

# ተግባርና ኃላፊነት

6. <u>የባህል ተቋማት የወል ተግባርና ኃላፊነት</u>

የባህል ተቋማት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፣

1) በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ የእጅ ንፅህና መጠበቂያ ግብዓቶችን የማቅረብ፤ ይህንን የሚቆጣጠር ሰራተኛ መመደብ እና መከታተል፣
2) ለሰራተኞች እና የጥበብ ባለሙያዎች በቂ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች ማቅረብ፣
3) በእንግዶች መቀበያ እና በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት አካባቢ በሰራተኞች መካከል እንዲሁም በሰራተኞች እና በተገልጋይ መካከል ርቀትን ማስጠበቂያ መከለያዎች ማዘጋጀት፣
4) በመግቢያ እና መውጫ በሮች አካባቢ የተገልጋይ ወይም የታዳሚ መቆያ ስፍራ እና የአካላዊ ርቀት መጠበቂያ ምልክት ማድረግ፣
5) በመግቢያ እና መውጫ አካባቢ አካላዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ በቂ መተላለፊያ እንዲኖር ማድረግ ፣
6) የፀረ-ተህዋስ መርጫ ግብዓት በማሟላት ተቋሙን ማጽዳት፤
7) የኮቪድ-19 የመከላከያ፣ የጥንቃቄ እና ደህንነት እርምጃዎችን ለተገልጋይ ግልጽ በሆነ ስፍራ መለጠፍ፤
8) ከአገልግሎት በፊት የአዳራሹ ውስጣዊ ክፍሉንና የመግቢያና መውጫ በሮች የፀረ-ተህዋስ ርጭት እና መጠቀሚያ ቁሳቁሶች በሳኒታይዘር አልኮል ማፅዳት፤

9) ደረጃውን የጠበቀ የሰውነት ሙቀት መለኪያ መሳሪያ በማዘጋጀት ሰራተኞችና ተገልጋዮች ወደ ተቋማቱ ከመግባታቸው በፊት ሙቀታቸውን መለካት እንዲሁም ከ38 ዲግሪ በላይ ሙቀት ሲኖር በመለየት ለጤና ተቋማት ማሳወቅ፤

10) የአገልግሎት ክፍያዎችን በባንክ ወይም ዘመናዊ አሰራርን በመጠቀም የመቀበል፤ ይህ ካልተቻለ ተጨማሪ የክፍያ መስኮቶች በማዘጋጀት የሰዎች ጥግግትን መቀነስ፤

11) የመመሪያውን አፈጻጸም በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ለሰራተኞችና ለተገልጋዮች የመስጠት፤

12) በአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ውስጥ በቂ አየር እንዲተላለፍ ማድረግ፤

13) በመፀዳጃ ቤቶች አካባቢ የሰዎች መተፋፈግ እንዳይኖር ተገቢ ክትትል ማድረግ፤

14) በኮቪድ-19 የጥንቃቄ እርምጃዎች መሰረት ተገቢውን የቆሻሻ የአወጋገድ ሥርዓት በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል፡፡

15) ተገልጋዮች በተገቢው አካላዊ ርቀት የሚጠቀሙበትን ግልጽ ምልክቶች ማስቀመጥ፤ አፈጻጸሙንም መቆጣጠር፤

16) የጥንቃቄ እና ደህንነት እንዲሁም የንፅህና አጠባበቅ ስርዓት ማሻሻያ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ፣

17) ይህንን መመሪያ በማይቃረን መልኩ የሚሰጡትን አገልግሎት ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ የራሳቸውን የጥንቃቄ እና ደህንነት መመሪያ የማዘጋጀት፤

## 7. <u>የሰራተኞችና የተገልጋዮች ግዴታ</u>

የባህል ተቋማት ሰራተኞችና ተገልጋዮች የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-

1) የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከላከያ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የማክበርና የመፈጸም፤
2) በማንኛውም ጊዜ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሎች ማድረግና የግል የእጅ ማጽጃ መያዝ፤
3) በተቋሙ ውስጥ ሲንቀሳቀሱም ሆነ ሲቀመጡ አካላዊ ርቀትን መጠበቅ፤
4) ወደ ተቋሙ ከመግባት በፊት የሰውነት ሙቀት ልኬት ማከናወን፤
5) በመግቢያ በሮች በሚቀመጥ የጫማ ማፅጃ ኬሚካል መጠቀም፤
6) የቁሳቀስ ንክኪ እና ቅብብሎሽ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ፤
7) በክፍያ ወቅት የሚኖር ንክኪ ለመቀነስ በሰጪም ሆነ ተቀባይ በኩል ከክፍያ በፊት እና በኃላ በሳኒታይዘር/አልኮል በተደጋጋሚ እጅን ማፅዳት፣

8) ማንኛውም የተቋሙ ሰራተኛ ወይም ተገልጋይ የህመም ስሜት ሲሰማው ለተቋሙ በማሳወቅ በቤት መቆየት የወረርሽኙ ምልክት ከታየ ለጤና ተቋማት ማሳወቅ፤

## 8. <u>የአብያተ-መጻሕፍት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 6 እና በአንቀፅ 7 የተገለፁት እንደተጠበቁ ሆነው አብያተ-መጻሕፍት የሚከተሉት ልዩ ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

1. በአንድ ጊዜ ማስተናገድ ከሚችለው መጠን በ50% ቀንሶ በመቀመጫዎች መካከል አካላዊ ርቀትን በመጠበቅ ለአንባቢያን አገልግሎት መስጠት፤
2. ከአገልግሎት በፊትና በኋላ ወንበሮችን፣ ጠረጴዛዎችን፣ መደርደሪያዎችን እና ለዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት የሚውሉ ኮምፒዩተሮችን በፀረ-ተህዋስ ማጽዳት፤
3. ያልተገባ የሰዎች መሰባሰብን ለመቀነስ እንዲቻል በቤተ-መጽሐፍት መግቢያ አካባቢ የሚከናወኑ የግብይት እና የተለያዩ ቁሳቁሶች ሽያጭ መከልከል ፡፡
4. የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የመከላከል ተግባርን የሚደግፍ ተገቢ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

## 9. <u>የአስነባቢዎች ወይም ሰራተኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 6 እና በአንቀፅ 7 የተገለፁ በግለሰብ እና በተቋም ደረጃ የሚተገበሩ የወል ኃላፊነት እና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

1) በእንግዳ መቀበያ ስፍራ በተገልጋዩ እና በአስነባቢው መካከል በቂ ርቀርት እንዲኖር ማድረግ፤
2) በመታወቂያ ካርድ ቅብብሎሽ ወቅት አካላዊ ርቀትን መጠበቅ እና ከንክኪ በኋላ እጅን በሳኒታይዘር/አልኮል ማፅዳት፤
3) የተነበቡ መፅሃፍትን ለ24 ሰዓት በተለየ መደርደሪያ በማቆየት በተከታዩ ቀን ለአገልግሎት ማዋል፡፡

## 10. <u>የአንባቢዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው አንባቢያን የሚከተሉት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡-

1) ከንባብ በፊት እና ቦኃላ እጅን በሳኒታይዘር (አልኮል) ማፅዳት፤
2) በቤተ-መጻሕፍቱ ውስጥ የሚተገበሩ በዚህ መመሪያ መነሻነት የተዘጋጁ ተጨማሪ ህግና ደንቦች ተፈፃሚ ማድረግ፤
3) አካላዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ ለመቀመጥ በተፈቀዱ ቦታዎች ብቻ መገልገል፤
4) የተጠቀሙበትን መጻሕፍ ተለይቶ በተዘጋጀ መደርደሪያ ማስቀመጥ፡፡
5) የግል የኤልክትሮኒክስ መገልገያዎችን ይዞ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

## 11.<u>የቤተ-መዘክር እና ጋለሪ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 6 ላይ የተገለፁ በግለሰብ እና በተቋም ደረጃ ተፈፃሚ የሚሆኑ ተግባር እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

1) ሙዝየሙ/ጋለሪው ከዚህ ቀደም በአንድ ጊዜ ማስተናደግ ከሚችለው መጠን በ50% በመቀነስ እና በጎብኚዎች መካከል አካላዊ ርቀትን ጠብቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ማዘጋጀት፣
2) የቡድን ጉብኝቶች የማይበረታታ ሲሆን ፣ ጎብኝዎች በቡድን የሚመጡበት ሁኔታ ሲከሰት በአነስተኛ መጠን ቡድኖች በመከፋፈል እንዲጎበኙ ማድረግ ፡፡

## 12.<u>የቤተ መዘክር ወይም የጋለሪ ሰራተኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 የተደነገገው የወል ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የቤተ-መዘክር ወይም የጋለሪ ሰራተኞች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

1) ጎብኚዎች በቤተ-መዘክሩ ወይም በጋለሪው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ከእጅ ንክኪ በጸዳ መልኩ እንዲጎበኝ ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ፤
2) ከጎብኚዎች ጋር የሚኖር አካላዊ ርቀትን ጠብቆ አገልግሎት መስጠት፤

## 13.<u>ትዕይንት ማሳያ ተቋማት ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 የተደነገነው እንደተጠበቀ ሆኖ የትዕይንት ማሳያ ተቋማት የሚከተሉት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

1) ተቋሙ ያስተናግድ ከነበረው የተገልጋይ ቁጥር አንድ አራተኛውን ብቻ በማስተናገድ የአገልግሎት ክፍያውን በአራት እጥፍ በማስላት አገልግሎቱን መስጠት፡፡
2) በትዕይንታዊ ጥበባት ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ወቅት መሰረታዊ የኮቪድ-19 የጥንቃቄ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤
3) ትዕይንቶች በሚቀርቡበት ወቅት በአቅራቢ እና በታዳሚ መካከል አካላዊ ርቀት ማስጠበቂያ መከለያ ማዘጋጀት፤
4) በትዕይንት ማቅረቢያ ስፍራዎች በቂ መተላለፊያ ቦታ እንዲኖር ማድረግ፤
5) በትዕይንት ማቅረቢያ አዳራሾች ውስጥ የምግብና መጠጥ መስተንግዶ አገልግሎቶችን መከልከል፤
6) የተከታታይ ትዕይንቶች የጊዜ መርሃ-ግብር መካከል በቂ የጊዜ ልዩነት እንዲኖር በማድረግ በመውጫ እና መግቢያ ወቅት የሚፈጠር ንክኪ መቀነስ፤

14.<u>የጥበብ ሥራ አቅራቢዎች ኃላፊነት</u>

1) ጥበባትን በመድረክ የሚያሳዩ/ተዋንያንን በተቋሙ ውስጥ ርቀትን ጠብቀው እስከ ዝግጅታቸው ፍጻሜ ድረስ መቆየት አለባቸው፣
2) ትዕይንት/ሙዚቃ አቅራቢዎች እና ተወዛዋዦች ከታዳሚው ጋር የሚኖር አካላዊ ርቀትን ጠብቀው ስራቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3) አካላዊ ንክኪን የሚጠይቁ ትዕይንቶች ማቅረብ የግድ ከሆነ አቅራቢዎች ትዕይንት ከማቅረባቸው 1 ቀን በፊት የኮቪድ-19 ምርመራ በማካሄድ ውጤታቸው ከኮቪድ-19 ነፃ መሆናቸው ተረጋግጦ መሆን አለበት፡፡

15.<u>መድረክ እና ከመድረክ ጀርባ የሚፈፀሙ ተግባራት</u>

1) ከላይ በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በልምምድ ወቅት እና በትዕይንት ወቅት አቅራቢዎች አካላዊ ንክኪን በሚቀንስ ሁኔታ በመካከላቸው የ2 ሜትር እና በላይ ርቀት ሊኖራቸው ይገባል፣
2) የልምምድ እና ዝግጅት ስፍራዎች ያልተጨናነቁ እና አካላዊ ርቀት በጠበቀ መልኩ ማከናወን የሚያስችል ቦታ ማዘጋጀት፣
3) የመድረክ መጠቀሚያ ቁሳቁሶች (የመብራት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ የድምጽ እና ምስል ሲስተሞች) እንዲሁም የመድረክ ግንባታ ስራዎች ተገቢውን ርቀት በመጠበቅ እና ቁሳቁሶችን በሳኒታይዘር በማፅዳት መጠቀም፣

4) በተዋንያን እና ተወዛዋገ‍ሮች መካከል የአልባሳት እና ጌጣጌጥ ቅይይር እንዳይኖር ማድረግ፣
5) የቁሳቁስ ቅያሬ ግዴታ በሚሆንበት ወቅት በሳኒታይዘር በማፅዳት መጠቀም፣
6) በፋሽን ትርዒት ወቅት የሚኖር የአልባሳት እና ጌጣጌጦች ቅያሬ ከንክኪ የፀዳ እና የጋራ መጠቀሚዎችን በሚቀንስ መልኩ ማከናወን፣
7) የጥበብ ስራዎችን ለሚያቀርቡ አርቲስቶች የሚሰጡ ሽልማቶች በአካል ንክኪ ሳይኖር በሚዘጋጅ ክፍት ማስቀመጫ ቦታ ላይ ማድረግ፣
8) የታዳሚዎች መቀመጫ ቦታዎች ከጥበብ ስራ አቅራቢዎች /መድረክ/ ከ2 ሜትር እና በላይ መራቅ ይኖርባቸዋል፡፡
9) በአዳራሽ ውስጥ መድረክ ላይ ወጥቶ ከጥበበኞች ጋርም ሆነ ከሌላ ታዳሚ ጋር ንክኪ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 16.<u>በሰርከስ ማሳያዎች መፈፀም ያለባቸው ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ለሰርከስ ትርኢት ማሳያ አልባሳት እና ቁሳቁስ አጠቃቀም ጥንቃቄ በተመላበት መልኩ ማከናወን፣
2) በግል የሚሰሩ፣ ንክኪ አልባ እና አካላዊ ርቀትን የጠበቀ የጥንድ ወይም የቡድን የሰርከስ ትርኢት ማቅረብ፤
3) አካላዊ ንክኪን የሚጋብዙ ትዕይንቶች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ከታመነ አቅራቢዎቹ ከአንድ ቀን በፊት የኮቪድ-19 ምርመራ በማድረግ ከበሽታው ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው ቢኖርም ማንኛውም የትዕይንት አቅራቢ ከታዳሚዎች ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ እንዲኖራቸው አይፈቀድም፡፡

## 17.<u>የከበራ አዘጋጅ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የከበራ መርሐ ግብሮችን እንዲያዘጋጅ በህግ ፍቃድ የተሰጠው አካል የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባወጣው መመሪያ አንቀጽ 23 የተጠቀሱትን ተግባራት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

## 18.<u>የከበራ ተሳታፊዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ከተጠቀሱ በግለሰብ ደረጃ የሚፈፀሙ የወል ተግባር እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

1) ወደ ከበራው ቦታ ለመገኘት የሚያስፈልግ የይለፍ ወረቀት ወይም ባጅ ይዞ መገኘት፣
2) ከሰዎች ጋር ከሚኖር ጥግግት እና ንክኪ ራስን መቆጠብ ፣
3) በዝግጅቱ አካላዊ ርቀትና ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማክበር፤
4) በኩነቱ አስተባባሪዎች የሚተላለፉ የጥንቃቄ መመሪያዎችን ተግባራዊ የማድረግ፡፡

19 . **<u>የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) መመሪያውን ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት የማስገንዘብ እና ተፈፃሚ እንዲሆን የመደገፍ እና የመከታተል፣
2) የመመሪያውን አፈጻጸም የሚከታተልና ተገቢውን ድጋፍ የሚሰጥ ግብረ-ሃይል በማደራጀት ማሰማራት፤
3) መመሪያውን ተፈፃሚ በማያደርጉ አካላት ላይ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበትን አግባብ የማመቻቸት፤
4) የመመሪያውን አፈጻጸም የመገምገምና ተገቢውን ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ የመስጠት፤
5) በመመሪያው አተገባበር ዙሪያ ከክልል ባህል እና ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በቅንጅት የመስራት፣

20. **<u>የክልል ባህልና ቱሪዘም ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ይህንን መመሪያ ተፈፃሚ ለማድረግ የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖርባቸዋል፡፡

1) ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ አፈጻጸሙን ለመከታተል ተገቢውን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
2) የመመሪያውን አፈጻጸም የሚከታተልና የሚገመግም ግብረ-ሃይል በየአስተዳደር እርከኑ የማዋቀርና ስራቸውን የመከታተል፡፡

3) መመሪያውን በተመለከተ በየደረጃው ላሉ የባህል ተቋማት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የመስራት፣

4) የመመሪያውን አተገባበር በተመለከተ ተገቢውን ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማ እና ቁጥጥር የማድረግ ፣

5) የመመሪያውን አፈጻጸም በሚያደናቅፉ አካላት ላይ ተገቢ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበትን አግባብ የማመቻቸት፤

6) የመመሪያው አፈፃፀም በተመለከተ ለሚኒስቴሩ ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

21. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም በሀገሪቱ የሚገኙ የባህል ተቋማትና አስፈጻሚ አካላት ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

22. **<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>**

ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ በአግባቡ ተፈፃሚ በማያደርጉ አካላት ላይ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

23. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

24. **<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከህዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሂሩት ካሳው ወንድም (ዶ/ር)
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ሚኒስትር